# <u>እብዱ</u>

አባ ጆሌ . . . አባ ጆሌ
ባለ ዛሩ . . . ባለ ቆሌ

አባ ቡቱ . . . አባ ዳማ
ቢፈልጡትም የማይደማ

ልዩ ፍጥረት አባ አበዶ
ዝብርቅርቁን አለም ወዶ
ወይም ደግሞ ተገድዶ

በሄደበት ሁሉ እንግዳ
ለሰማይ ለምድር ባዳ

ህልቆ መሳፍርት ህጻናት
የሚያጅቡት . . . የሚርቁት
የሚወዱት . . . የሚጠሉት
የሚቀርቡት . . . የሚሸሹት

እብዱ እብዱ እብዱ ሚሉት
በሩቅ የሚያሾፉበት
በቅርብ የሚተፉበት

አባ ቱባ
ቤት የሌለው . . . ከቶ ቤቱ የማይገባ

ያገኘውን ለቅሞ በልቶ
በወደቀበት ተኝቶ
በዚያው ደግሞ ተጸዳድቶ

አባ  ጆሌ . . እርሱ እኮ አባ ጆሌ
እግሩ ነድዶ በሞያሌ

ለገበርኪ ለኢያሱ
አንጀራ ሞልቶ በኪሱ
በቅማል ተወርሮ ራሱ
ተሰባበሮ ወልቆ ጥርሱ

ዘመድ የለው
የሚያስጠጋው
እንደምን አደርክ የሚለው

እርሱ ግን አባ መርገጥ
አባ ማየት አባ ማፍጠጥ

ግድ የለውም
አይገደውም

ቀንና ለሊት ሳይፈራ
ከሰማይ ከምድር ጋራ
የሚያወራ

ከመላእክት ጋራ አብሮ
አውሰውት ክንፋቸውን. . .በክንፋቸው ከንፎ
በርሮ

ሰባቱን ሰማያት አልፎ

ከጻድቃን ጋር ተሰልፎ
አብሮ በልቶ
ካማላክት ጋር ፍርድ ሰጥቶ
አንዱን አስሮ አንዱን ፈትቶ

አድዋና ካራማራ
እልፍ ወታደር እየመራ

በሰይፉ እሳት እልፍ ቆልቶ
አሸንፎ ሁሉን ረትቶ

አባ ፈጣን አባ ቀስቱ
ተሸፍኖ በቡቱቱ

የሚስቅ አያመመው
እየፈጀው . . .

ነውር የማያውቅ . . . ራቁት ገላ መውጣቱን
ባውራ ጎዳና መሸናትን

መጋለጡ መግለጥለጡ
አባ ጆሌ ምኑ ቅጡ

አባ ቱባ . . . ሳይጠቃ እሚበቀል
ሲነካ ግን ችላ የሚል

ሲያመው አባ ጆሌ ሲያመው
የለ የሚያስታምመው

ሲርበው
የለም ቆርሶ የሚያጎርሰው

በራሱ ውስጥ ሃሳብ ፈልቶ
አንጎል ኩላሊቱን በልቶ
ሁለመናው ተበላሽቶ

አባ እብዱ እግር የለው
ቢኖረውም ውልግድግድ ነው

ወርቅ ቢለብስ አያምርበት
ሽቶም ቢሆን አይሸትልት
ከረፋበት . . .

ተውኝ ብቻ ያንተ ነገር
ተከድኖ ይቅር ያንተ ሚስጥር

ይቅር ተወው ይቅር ብቻ
ማረኝ ብቻ . . .
ተወኝ ብቻ . . .

ይቅር ብቻ ይቅር በለኝ
ቀኔ ቀንቶ ሲያቀንነኝ

እኔም አባ ቱባ ነኝ
እኔም አባ ጆሌ ነኝ
አባ ቡቱ ቡቱቱም ነኝ

ዘውዱ ሳህሉ
October 2007

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Zewdu Sahlu  for comments at*** *zewdu_michael@yahoo.com*